# POLICY BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

ተዛማጅ ምንጮች: ABA, ACA, ACF, BFA, COA-RA, COG-RA, DJA-RB, ECA, EGB-RA, EGF-RA, IGT-RA, IIB, IIB-RA, IKA, IKA-RA, ITA-RA, JHC, JHC-RA, JHF, JHF-RA, JOA-RA, KBA, KGA-RB

ኃላፊነት የሚመለከታቸው ክፍሎች፡- የቴክኖሎጂ አገልግሎት ክፍል፤ የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻል ክፍል፤ የመማር ማስተማር ክፍል

## የትምሕርት ቴክኖሎጂ/Educational Technology

I. ዓላማ

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) የመማር ማስተማርን ፋይዳ፣ እና የአሠራር ትግበራን ለማሻሻል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ዓላማ ባለው፣ ተገቢ፣ እና ስልታዊ በሆነ መንገድ በማዋሃድ ለመጠቀምና ለማስተዳደር የሚረዱ መመሪያዎችን ማዘጋጀት

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ቴክኖሎጂን በመጠቀም ረገድ ደህንነቱ በተጠበቀ እና ኃላፊነት በተሞላበት መልክ ለመግባባት፣ ለመተባበር፣ ለፈጠራ ክንውን፣ እና ፈጠራን በመጠቀም፣ አኳያ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን በመቀነስ፣ ማስተማርን፣ መማርን እና የስራ ክንውኖችን ለመደገፍ ፍትሃዊ ተደራሽነት እና እድል ለመስጠት ያለውን ቁርጠኝነት ዳግመኛ ማረጋገጥ።

II. ጭብጦች

በሜሪላንድ እና በመላው ዩናይትድ ስቴትስ በሚገኙ የትምህርት ዲስትሪክቶች ውስጥ የትምህርት ልህቀትን ለማበልፀግ በአገር አቀፍ እና በስቴት ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ኤጀንሲዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃላይ የተቀናጀ አሠራር ለመምራት የአፈጻጸም መስፈርቶችን አዘጋጅተዋል። እነዚህ መስፈርቶች በተማሪዎች፣ በአስተማሪዎች፣ በትምህርት መሪዎች እና በስራ ላይ ባሉ ሰራተኞች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ዲጂታል የመማሪያ መሳሪያዎችን አጠቃቀም ይመለከታሉ።
የሜሪላንድ ዲጂታል የመማሪያ መስፈርቶች ዲጂታል መረጃ እና የትምህርት ቴክኖሎጂን ደህንነቱ

የተጠበቀ፣ ህጋዊ እና ሥነ ምግባራዊ አጠቃቀምን በተመለከተ በፖሊሲዎች ውስጥ መተግበር ያለባቸውን ቁልፍ መርሆዎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ያመለክታሉ፣ ይህም የትምህርት ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም የትምህርት ግቦችን ስኬት ለማሻሻል፣ ተገቢ የሆኑ ዲጂታል መሳሪያዎችን ፍትሃዊ ተደራሽነት ለማረጋገጥ፣ እና ከቴክኖሎጂ እና ከመረጃ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ኃላፊነት የተሞላበት ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማሳወቅ የሚመራ የአጠቃቀም ስልት ነው።

III. አቋም

የማስተማርያ እና የአሠራር ፍላጎቶችን የሚደግፉ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች በፍጥነት እየተሻሻሉ ናቸው። ቦርዱ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም እንዲያውሉ ለማድረግ እና ጊዜው ያለፈበትን ቴክኖሎጂ በወቅቱ እና ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ ለመተካት ቁርጠኛ ነው። ቦርዱ የመሠረተ ልማት ፍላጎቶችን ካሉት የመገልገያ ሪሶርሶች ጋር በማመጣጠን፣ በተለይ ለትምህርት ተግባር ተለይተው የሚዘጋጁ አዳዲስ ፈጠራዎችን በስትራቴጂካዊ ቴክኖሎጂ እና በመሠረተ ልማት ፍላጎቶች ላይ በመመሥረት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ ይፈልጋል። የሚከተሉት መርሆዎች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶችን (MCPS) የማስተማር፣ የመማር፣ እና የአሠራር ሂደት ለመደገፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማጣመርይመራሉ።

A. ሥርዓተ ትምህርት፣ ማስተማር፣ እና የተማሪዎች ትምህርት የመቅሰም ማረጋገጫ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ ተማሪዎችን የትምህርት ግቦቻቸውን በመምረጥ፣ በማሳካት እና ብቃትን በማሳየት ረገድ ንቁ ሚና እንዲጫወቱ ያስችላቸዋል።

1. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በማስተማር፣ በሥርዓተ ትምህርት ዓላማዎች እና በመማር ሂደቶች ትክክለኛነት ላይ ስለሚኖራቸው አዎንታዊ አስተዋጽኦ እና ተጽዕኖ ግምገማ ይደረጋል።

2. በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚመረጡ ቴክኖሎጂዎች ኦሪጅናል፣ ትክክለኛ፣ እና የትምህርት ሥራዎችን በንቃት ለመሥራት የሚያስችሉ፤ እንደአስፈላጊነቱ ከፍተኛ ደረጃ አስተሳሰብን መገምገም፤ እና የአካዳሚክ ታማኝነትን ማበረታታት አለባቸው።

3. MCPS ሰራተኞችን እና ተማሪዎችን መረጃ ለማግኘት እና ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉትን የዲጂታል ሊተርሲ ክህሎቶችን ያሰለጥናቸዋል፤ መረጃዎችን ከዲጂታል የመረጃ ምንጮች ለማሰባሰብ የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠቀም በጥልቀት እንዲያስቡበት፤ እና የሁሉም ዲጂታል እና አናሎግ የመረጃ ምንጮች ትክክለኛነታቸውን እና ተዓማኒነታቸውን ይመረምራል።

4. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ሰራተኞች ለማስተማር እና የትምህርት አሠራር ዘዴዎችን ለመደገፍ የትምህርት ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም ሰብአዊ የማመዛዘን ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ፕሮፌሽናል ተማሪዎችን ማብቃት አለባቸው።

B. ሰው ሰራሽ አስተውሎት/አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (ለምሣሌ፦ Generative, Predictive, Agentic, Retrieval-augmented generation)። ቦርዱ–ስለ ሰው ሰራሽ አስተውሎት/አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) የአጠቃላይ ለውጥ አቅምን ይገነዘባል፣ ይህም መረጃን የማቀናበር፣ የመተንበይ፣ ወይም የመረጃ ሂደት ስርዓቶችን ጽሑፍ፣ ምስሎች፣ ኦዲዮ ወይም ቪዲዮ የመሳሰሉ ኦሪጅናል ይዘቶችን በማቅረብ የመማር ማስተማር ስራዎችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን እንደሚያካትት ይታወቃል። እነዚህ መገልገያ መሳሪያዎች በመምህራን የሚመራውን የትምህርት አሰጣጥ፣ ትክክለኛ ትምህርትን እና የስራ ፍሰት ማመቻቸትን ከመተካት ይልቅ፣ በመምህራን የሚመራ የትምህርት አቀራረብን ለመደገፍ የታሰቡ ናቸው።

1. የአልጎሪዝም ማዛባትን እና የተሳሳተ መረጃ አደጋዎችን ለመቀነስ፣ ቦርዱ MCPS እውነኛ እና ትክክለኛ የሆነ፣ ሥነ ምግባር ያለው የውሂብ ምንጭ እና ከተዛባ የመረጃ ምንጭ ከሚገኙ ውጤቶች ለመጠበቅ ምርጥ ልምዶችን ለማሳካት ለሁሉም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች መደበኛ የማጣሪያ ሂደት እንዲተገበር ያደርጋል።

2. ቦርዱ የግልጽነት፣ የእውነተኝነት፣ እና የፍትሃዊነት መርሆዎችን ለማክበር ቁርጠኛ ነው። ቦርዱ በሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) ተጽዕኖ በተፈጠሩ ይዘቶች ላይ ወሳኝ በሆነ ምርመራ የሰው ልጅ ቁጥጥር እንዲኖር ያልተቋረጠ ጥረት ያደርጋል።

3. የሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) የአጠቃቀም መመሪያን በመደገፍ፣ ማስተማርን፣ ትምህርትን በግል ለመማር፣ አስተዳደርዊ ስራዎችን ለማቀላጠፍ፣ እና የትምህርት እና የአሠራር ግብዓቶችን ተደራሽነት ለማስፋት አስፈላጊ የሆኑ የደህንነት እርምጃዎችን እና ሙያዊ ትምህርትን ፀተቀናጀ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መደገፍ አለባቸው።

4. በተማሪዎች የትምህርት ሥራ ላይ ንቁ፣ ትክክለኛ ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን፣ እና ስለ AI-ይዘት ግልጽነትን ለማረጋገጥ በተማሪዎች አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር ይደረጋል።

5. የተማሪዎችም ሆነ የሰራተኞች አስተዳደራዊ መመሪያዎች በየጊዜው መገምገም እና መከለስ አለባቸው።

C. የመረጃ ብትህውነት እና የመረጃ ደህንነት

ቦርዱ በቦርድ ፖሊሲ KBA፣ ስለሕዝብ መረጃ ላይ እንደተገለጸው የተማሪዎች እና የሰራተኞችን መረጃ ግላዊነት እና ደህንነት ለመጠበቅ እና የውሂብ አሰባሰብ፣ ግላዊነት፣

እና ደህንነቱ የተጠበቀ የውሂብ ቋት እና አያያዝን በተመለከተ ሁሉንም የሚመለከታቸውን የስቴት እና የፌዴራል ህጎች ለማክበር ቁርጠኛ ነው።

D. የመማር ዝንባሌዎች፣ ፍላጎቶች፣ እና ዘዴዎች

1. ቦርዱ የተማሪዎችን የተለያዩ የትምህርት ዝንባሌዎች ለመደገፍ፣ የተለያዩ ፍላጎቶችን ለመከታተልና ለማመቻቸት፣ እና የመደበኛ ትምህርትን ባለብዙ እርከን ጣልቃገብነቶች፣ ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት፣ እንዲሁም የተፋጠነ እና የበለፀገ ትምህርትን ለማመቻቸት እና ለማሟላት የተመረጡ ስትራቴጂካዊ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን አቅም ይገነዘባል።
2. የትምህርት አሰጣጥ ተግባሮች የትምህርት ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ከተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች እና አማራጮች ጋር በማመጣጠን ንቁ፣ አሳታፊ፣ ትርጉም ያለው እና ማህበራዊ መስተጋብር ያለው ትምህርትን መደገፍ አለባቸው። ይህን ለማድረግ፣ MCPS የተማሪዎችን የዕድሜ እና የእድገት ደረጃ ግምት ውስጥ ማስገባት እና የሰው ቁጥጥር የሚደረግበት ዲጂታል ይዘት ጋር የሚያሳልፈውን ጊዜ መከታተል አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ እና የተለያዩ የመማሪያ ዘዴዎችን ማመቻቸት እና ማቅረብ አለበት።
3. MCPS እንደአስፈላጊነቱ ፍትሃዊነትን ከማስፈን አኳያ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማል፣ እንዲሁም በቀላል የሚታዩ የግንኙነት ስጋቶችን ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች እንደዚህ አይነት የትምህርታዊ ቴክኖሎጂን ከትምህርት ቤት ውጭ በተናጠል እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ሊኖራቸው የሚገባቸውን ድጋፍ በጥንቃቄ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።
4. ቦርዱ ተማሪዎችን፣ መምህራንን እና ሌሎች የሥራ ባልደረቦችን ሁኔታ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ በቨርቹዋል ትምህርት ላይ እንዲሳተፉ የሚያስፈልጋቸውን ቴክኖሎጂ እና ድጋፍ ለመስጠት ቁርጠኛ ነው።

E. ፍትኃዊነት

1. MCPS ቴክኖሎጂን ከማስተማር እና ከትምህርታዊ ተግባራት ጋር በማዋሃድ፣ ከሚከተሉት የፍትሃዊነት መርሆዎች ጋር ያጣጥማል –
   a) የቦርድ ፖሊሲ ACA ፀረ መድሎአዊነት፣ ፍትሐዊነት፣ እና የብቃት ባህል
   b) በአሜሪካ ስለ አካል ጉዳተኞች ሕግ እንዲሁም ስለ ተደራሽነት በስቴት ሕጎችና ደንቦች ላይ እንደተገለጸው የስቴትና የፌዴራል መስፈርቶችን፤ እና
   c) ስለ ትምህርት ዩንቨርሳል ዲዛይን የተደራሽነት መስፈርቶች።
2. የዲጂታል መሳሪያዎች ስትራቴጂካዊ አጠቃቀም ተማሪዎች የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን በተመለከተ ያላቸውን የፍትሃዊነት አንድምታ እና ተማሪዎች የትምህርት ቴክኖሎጂን ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲጠቀሙ ሲጠየቁ ሊያጋጥሟቸው የሚችሏቸውን የተለያዩ ተግዳሮቶች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

F. በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ምርጫ እና ከትምህርት ቴክኖሎጂ ጋር ማጣመር

1. MCPS ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የትምህርት ፕሮግራሞችና ስራዎችን ለማከናወን ውጤታማ፣ ተገቢ፣ ዘላቂ እና የፋይናንስ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት ቴክኖሎጂን ለማግኘት እና ለመጠቀም ስልታዊ አቀራረብን መውሰድ አለበት።
2. ስለ ተማሪዎች ትምህርት ከሜሪላንድ መመዘኛዎች እና የቦርድ ፖሊሲዎች እና ግቦች ጋር በሚስማማ መልኩ፣ MCPS ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ የትምህርት ቴክኖሎጂዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምረጥ እና ከሚሰጡ ትምህርቶች ጋር ለማቀናጀት በማስረጃ ላይ በተመሰረቱ ስልቶች እና ዘዴዎችን ይተገብራል።
3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርታዊ ቴክኖሎጂ ሪሶርሶችን ከሚፈለገው የትምህርት ውጤቶች ጋር ያቀናጃል እና ይቆጣጠራል። በማስረጃ ላይ በተመሰረቱ ምርጥ የማስተማር ተሞክሮዎች – ይመራሉ
    a) አዳዲስ የትምህርት ቴክኖሎጂ ምርቶችን ማዘጋጀት እና/ወይም መለየት፣ መምረጥ እና ማግኘት፤ እና
    b) በቀጥታ ማስተማር፣ የተቀናጀ ትምሕርት፣ እና የርቀት ትምህርትን የሚያካትት በተለያዩ የትምህርት አቅጣጫዎች፣ ማስተማርን እና መማርን ለመደገፍ እና ለማዳበር የታለመ ግብ ያለው/አላማ ያለው ስትራቴጂያዊ የሆነ የሪሶርሶች ቅንጅት።

G. መልካም ሥነ ምግባር ያለው እና ኃላፊነት የተሞላበት አጠቃቀም

1. ቦርዱ ለተማሪዎችና ለአስተማሪዎች የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) የዲጂታል ትምህርት መስፈርቶችን ይደግፋል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፡-
    a) የቴክኖሎጂ እውቀት/ሊተርሲ ማለት የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በሚመለከት ከሌሎች ጋር በመተባበር እና በተናጥል የመሥራት ችሎታ ማለት ነው፤ እንዲሁም የመረጃ ተደራሽነትን፣ ማስተዳደር፣ ማዋሃድ፣ መገምገም፣ ፈጠራ፣ እና እውቀትን/መረጃን ለማስተላለፍ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት አኳኋን፣ በአግባቡ እና በብቃት መጠቀም ማለት ነው።
    b) የመረጃ እና የሚዲያ እውቀት/ሊተርሲ ማለት የመረጃ ይዘትን በተለያዩ ቅርጾች የመድረስ፣ የመተንተን፣ የመገምገም እና የመፍጠር ችሎታ ማለት ነው። ይህ በሁሉም የሚዲያ ገጽታዎች ላይ የመረጃን ምንጭ፣ ትክክለኛነት፣ ተዓማኒነት እና አድሎአዊነት ለመገምገም የሚያስፈልጉትን ወሳኝ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ያካትታል።
    c) ዲጂታል ዜግነት ማለት ግለሰቦች በቴክኖሎጂ የበለፀገ ማህበረሰብ ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ፣ ውጤታማ፣ እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲሳተፉ የሚያስፈልጉ የብቃት፣ የሥነ ምግባር፣ እና የባህሪ ቅንጅት ማለት ነው።
    d) የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማለት ዲጂታል ስራዎችን እና የደህንነት ፕሮቶኮሎችን የሚደግፉ መሰረታዊ ሃርድዌር፣ ሶፍትዌር፣ እና የኔትወርክ ስርዓቶች ማለት ነው።

2. ቦርዱ MCPS የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትን እና በቴክኖሎጂ፣ በመረጃ እና በሚዲያ ሊተርሲ እና በዲጂታል ዜግነት ላይ ግልጽ የሆነ መመሪያ መስጠት ይፈልጋል፤ ይህም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ተማሪዎች እና ሰራተኞች ቴክኖሎጂን በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ሰጪ እና የእውቀት ፈጣሪዎች አድርገው በአግባቡ፣ በዓላማ፣ እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል።

3. ተማሪዎች እና ሠራተኞች መብቶችን፣ ኃላፊነቶችን፣ እና የመኖር፣ የመማር፣ እና የመሥራት እድሎችን እርስ በርስ በተገናኘ የዲጅታል ዓለም፣ ጤናማ፣ ህጋዊ፣ እና ስነምግባር የተሞላበት አጠቃቀምን መተግበር እንዳለባቸው ቦርዱ ያስገነዝባል። ተማሪዎች እና ሰራተኞች በመረጃ እውቀት እና በዲጂታል ዜግነት ዙሪያ በመማር ላይ መሳተፍ አለባቸው፤ ይህም የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል—
   a) ዲጂታል መለያቸውን ማዳበርና ማስተዳደር እንዲሁም በዲጂታል ግንኙነት ላይ የግል መረጃዎችን ሲፈጥሩ፣ ሲያገኙና፣ ሲያሰራጩ በአስተዋይነት ወይም በተዘዋዋሪ ሊያቀርቡት የሚችሉትን የግል መረጃ (ዲጂታል "አሻራ" በመባልም ይታወቃል) የአጭር እና የረጅም ጊዜ አንድምታዎችን እንዲያውቁ ማድረግ፤
   b) ማህበራዊ ግንኙነቶችን ጨምሮ ቴክኖሎጂን ሲጠቀሙ አዎንታዊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ህጋዊ እና የሥነ ምግባር ባህሪን መከተል ይጠበቅባቸዋል፤
   c) የሌሎችን ግላዊነት እና ደህንነት እና የአእምሮ ፈጠራ ንብረትን በአግባቡ እና በህጋዊ መንገድ የመጠቀም እና የመጋራት ግዴታዎችን መረዳት እና ማክበር፣
   d) የዲጂታል ግላዊነት እና ደህንነትን ከመጠበቅ አኳያ የራሳቸውን የግል መረጃ ያስተዳድራሉ፣ የኦንላይን ዳሰሳዎችን ለመከታተል ሊያገለግሉ የሚችሉ የውሂብ-አሰባሰብ ቴክኖሎጂዎች እንዳሉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፤
   e) የግል መለያ መረጃዎችን እና ሌሎች ሚስጥራዊ መረጃዎችን አጠቃቀም እና አያያዝ በተመለከተ ሌሎችን ስለሚጎዳበት ሁኔታ የሚገልፅ መመሪያ እና ሙያዊ ትምህርት ያገኛሉ።

H. ከባቢያዊ ስጋቶች

ከቦርድ ፖሊሲ ECA፣ ዘላቂነት ጋር በሚስማማ መልኩ፣ ቦርዱ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም የሚያስከትለውን የአካባቢ ተጽዕኖ ለመቀነስ ቁርጠኛ ነው። ከ MSDE የከባቢ ሊተርሲ መስፈርቶች ጋር በሚስማማ መልኩ፣ MCPS ሰዎች የሚያደርጉት ተግባር በአካባቢ ላይ ስለሚፈጥረው ተጽእኖ ተማሪዎች እንዲረዱ እድሎችን ይፈጥራል።

1. የኤሌክትሮኒክስ ማስወገድ ብክነትን ለመቀነስ MCPS የሃርድዌርን የረጅም ጊዜ አገልግሎት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።
2. MCPS ሰራተኞችና ተማሪዎች አላስፈላጊ የሀብት አጠቃቀምን እና ከአርቲፊሻል

ኢንተለጀንስ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ የሀብት ፍጆታን ለመቀነስ እንዲያስቡበት ይበረታታሉ።

**የአተገባበር ስልቶች**

A. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ደንቦች ወይም ሌሎች አስተዳደራዊ ሂደቶችን በየጊዜው ያዘጋጃል እና ያሻሽላል።

B. MCPS ከማህበረሰቡ እና ከዕለታዊ ስራዎች ጋር ትምህርትን፣ የስራ ሂደቶችን እና የኮሙኒኬሽን ተግባር ለመደገፍ የሚከተሉትን ጨምሮ ሁሉን አቀፍ ተግባራዊ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ያቀርባል—

1. ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች፣ የሚዲያ ማዕከላት እና ቢሮዎች ተገናኝተው ተገቢ መሠረተ ልማት እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ መሰረታዊ መስፈርቶችን ማዘጋጀት፣ ይኼውም ሁሉም ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ለማስተማር፣ ለመማር፣ ለአስተዳደር እና ለዕለታዊ ስራዎች ፍትሃዊ እና ቀላል ቴክኖሎጂዎችን እንዲያገኙ ማስቻል ይሆናል፤
2. ለሲስተሞችና ለኔትወርኮች ሰፊ ተደራሽነትን ማመቻቸት፣ በእንደዚህ አይነት ሲስተሞችና ኔትወርኮች በኩል ተደራሽ የሆኑ ሠነዶችን ደህንነት መጠበቅ። በሁሉም የሚመለከታቸው ህጎች መሠረት ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ መስፈርቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤ እና
3. የመማሪያ ክፍሎችን ስለማገናኘት ትብብር ግንኙነትን ለማዳበር እና ለማስፋፋት ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ ከትምህርት ቤቶች ሁኔታ ባሻገር የመማር እድሎችን ለመስጠት እና በተማሪዎች፣ በመምህራን፣ በሰራተኞች፣ በወላጆች/በአሳዳጊዎች እና በማህበረሰቡ አባላት መካከል እንደአስፈላጊነቱ የትብብር ግንኙነቶችን ማዳበር

C. ቴክኖሎጂ የትምህርት ግቦችን ለማራመድ እንደ ስትራቴጂካዊ ግብዓት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

1. የትምህርት ቴክኖሎጂን በሚመለከት ኃላፊነት ያላቸው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ክፍሎች እርስ በእርስ እና ከካውንቲ፣ ከስቴት እና ከብሔራዊ ቡድኖች ጋር በመተባበር፣ ወቅታዊ፣ የላቀ እና አዳዲስ የቢዝነስ ቴክኖሎጂዎችን ለመመርመር እና አስፈላጊ የሆነ ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ አፕሊኬሽኖችን ለመለየት ወይም ለማዳበር አብረው መሥራት አለባቸው።
2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎች መማር እና የተማሪዎች ስኬታማነት ዓላማን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በመቆጣጠር ረገድ በርካታ-መስፈርቶችን ይተገብራል። ቀጣይነት ያለው የተማሪዎች ግስጋሴን መቆጣጠር ተማሪዎች ወቅታዊ እና ተገቢውን ድጋፍ ማግኘታቸውን፣ ትኩረት ያለው ጣልቃገብነትን፣ የተፋጠነ፣ እና የዳበረ ድጋፍ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። በተወሰኑ እርምጃዎች ላይ የተማሪዎችን የትኩረት ቡድኖች አፈፃፀም በተመለከተ አጠቃላይ

ሪፖርት ማድረግ ለፍትሃዊነትና ቀጣይነት ያለው ተጠያቂነት፣ ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽነት፣ የተለያየ እድል እና ስኬት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ትንታኔ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

3. MCPS የተማሪዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች የሚያሟሉ የርቀት ትምህርት ወይም የጣምራ ትምህርትን ጨምሮ፣ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ የተማሪዎችን ትምሕርታዊ እንቅስቃሴዎች ለመደገፍ የትምህርት ቴክኖሎጂን ለመገምገም፣ ለማዳበር እና/ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ለመምረጥ መደበኛ የማጣራት ሂደት ይጠቀማል።

4. MCPS የሚያስፈልገውን ብቃት በመለየት ለሰራተኞች ሰብአዊ ማመዛዘንን፣ የማስተማር አመራርን ለመጠበቅ እና ቴክኖሎጂን ከትምህርት ጋር በአግባቡ ለማዋሃድ የሚያስፈልጉ ተገቢ የሙያ ትምህርት እና የድጋፍ ስልቶችን ያቀርባል፣ ይኼውም ከስቴት እና ከፌዴራል ተደራሽ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁሶች መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው።

5. የመማሪያ መጽሐፍት፣ ዲጂታል መሳሪያዎች፣ የህትመት እና ዲጂታል የመማሪያ ግብዓቶች በስትራቴጂካዊ መንገድ እየተመረጡ፣ ለግለሰብ የትምሕርት ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግ አለባቸው።

D. የውሂብ ግላዊነት እና ደህንነት

1. ቦርዱ ማንኛውንም የማስተማሪያ እና የአሠራር ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የውሂብ ግላዊነት እና ደህንነት አስፈላጊ መስፈርቶች የሚሆኑበትን ጥብቅ የማጣሪያ ሂደት ያዘጋጃል።

2. MCPS ምርቶችና ሻጮቹ የሚመለከታቸውን የፌዴራል እና የስቴት ህጎችን እንዲያከብሩ ይፈልጋል፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የፌዴራል የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህግ (FERPA)፣ የፌዴራል የህፃናት የኦንላይን የግላዊነት ጥበቃ ህግ (COPPA) እና የሜሪላንድ የኦንላይን የውሂብ ግላዊነት ህግ (MODPA)።

3. MCPS የዲጂታል መረጃ እና ቴክኖሎጂን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ህጋዊ እና ሥነ ምግባራዊ አጠቃቀምን የሚያበረታታ፣ ሞዴል መመሪያዎችን ያወጣል፣ እንዲሁም ተገቢ ያልሆነ የእንደዚህ አይነት መረጃ አጠቃቀምን ለማስወገድ፣ እና ለመከላከል ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

    a) MCPS መረጃ እና የመረጃ ሲስተሞችን ካልተፈቀደ ተደራሽነት፣ ካልተፈቀደ አጠቃቀም፣ ግላዊ መረጃን ይፋ ከማድረግ፣ ከማስተጓጎል፣ ከማሻሻል ወይም ከማጥፋት ለመጠበቅ ተገቢ ሪሶርሶችን ያዘጋጃል፣ እንዲሁም እንደዚህ አይነት መረጃዎችን ለማስተማር፣ ለትምህርት እና ለሥራ ሂደት በአግባቡ ተደራሽ ያደርጋል።

    b) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ ተማሪ እና የሠራተኛ መረጃ/ዳታ ግላዊነትን ለመጠበቅ-ለመከላከል የተለየ የአሠራር ሲስተሞችን፣

ፕሮቶኮሎችን፣ እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

E. MCPS የሁሉንም ተማሪዎች የተለያዩ ዝንባሌዎች እና ፍላጎቶች ለማሟላት የትምህርት ቴክኖሎጂን፣ ዲጂታል ይዘትን እና የመማር እድሎችን በመጠቀም የላቀ ትምህርት ለመቅረጽ፣ ለማራመድ እና ለማፋጠን ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር መሳተፍ አለበት። MCPS ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች እና ከማህበረሰብ ቡድኖች ጋር በመተባበር ተማሪዎች የትምህርት ቴክኖሎጂን በአግባቡ እንዲያገኙ እና እንደዚህ አይነት ቴክኖሎጂን በትምህርት ቤቶች ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲጠቀሙ ድጋፍ ይሰጣል።

IV. የሚጠበቁ ውጤቶች

A. በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ትምህርትና አሠራር ውስጥ፣ እንዲሁም የተማሪዎችን አፈጻጸምና ስኬት፣ የሰራተኞችን ምርታማነት እና የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ውጤታማነት ለመደገፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ፣ በብቃት፣ በዘላቂነት እና በፍትሃዊነት የተቀናጁና የተጣለጡ መሆን አለባቸው።

B. አዳዲስ የትምህርት ቴክኖሎጂዎችን ማዘጋጀት እና/ወይም መምረጥ የቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንቶች ፍትሃዊነት፣ ተደራሽነት፣ እና የትምህርት ቴክኖሎጂን በትክክለኛ የሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ላይ በተገቢው ሁኔታ በማቀናጀት ያለውን አንድምታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

C. ሰራተኞችና ተማሪዎች የቴክኖሎጂ መገልገያዎችን በአግባቡ፣ በብቃት እና በኃላፊነት መጠቀም አለባቸው።

D. ሁሉም ትምህርት ቤቶችና ቢሮዎች ባላቸው ዲጅታል የትምሕርት መገልገያዎች መጠን ፍትሃዊና ተገቢ የሆነ የመሠረተ ልማትና የመገናኛ አቅም ሊኖራቸው ይገባል፣ እናም MCPS እንደዚህ ያሉ የመሠረተ ልማትና የኮሙኒኬሽን ብቃታቸውን በየጊዜው ይገመግማል።

V. ክለሳ እና ሪፖርት

A. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት የዚህን ፖሊሲ አፈፃፀም መከታተል፣ መገምገም፣ እና በየዓመቱ ለቦርዱ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

B. ይህ መመሪያ በትምህርት ቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት እና በቦርድ ፖሊሲ BFA፣ የፖሊሲ ቀረጻመርሕ መሰረት ይገመገማል።

ተዛማጅ ምንጮች፡- Family Educational Rights and Privacy Act, 20 U.S.C §1232g; Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA), 20 U.S.C. §1232h 34 CFR Part 98, (2000 and Supp IV 2004); Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, as amended, 29 U.S.C. Sec 794; Americans with Disabilities Act (ADA), 42 U.S.C. 12131 et seq;

Children’s Internet Protection Act (CIPA), 47 U.S.C. §254(h)(5)(B) -(C), 254(l); Children’s Online Privacy Protection Act of 1998 (COPPA), 15 U.S.C.6501-6505, 16 CFR Part 312; 2024 National Educational Technology Plan: A Call to Action for Closing the Digital Access, Design, and Use Divides, U.S. Department of Education, Office of Educational Technology, January 2024; Public Information Act of Maryland, Ann Code of Maryland, General Provisions Article §§4-101 through 4-601; Maryland Student Data Privacy Act of 2015, Ann Code of Maryland, Education Article, §4-131 and 7-443; Code of Maryland Regulations §13A.03.02.03.B(8) and §13A.06.05.02-.04, .06; Maryland Digital Learning Standards for Students and the Maryland Digital Learning Standards for Educators, Maryland State Department of Education (MSDE), May 2019; Technology Education Standards: Grades 6-12, MSDE, January 2016; Health and Safety Best Practice Guidelines: Digital Devices, MSDE, July, 2019; International Society for Technology in Education Standards Administrators, Education Leaders, Educators, and Students; MCPS Student Code of Conduct.

**ስለ ፖሊሲው ታሪክ፦**

ከውሳኔ ቁጥር 863-93 በፊት፣ ይህ ጉዳይ በሚከተሉት መመሪያዎች ይተዳደር ነበር፡- የኮምፒዩተር ትምህርት አጠቃቀም፣ በውሳኔ ቁጥር 995-83፣ ዲሰምበር 13, 1983 ፀደቀ፣ በውሳኔ ቁጥር 333-86፣ ጁን 12, 1986 እና በውሳኔ ቁጥር 458-86፣ ኦገስት 12, 1986 ተሻሻለ፤ በውሳኔ ቁጥር 863-93፣ ዲሰምበር 8, 1993 ተሽሯል። ፖሊሲ IGS በውሳኔ ቁጥር 863-93 ዲሰምበር 8, 1993 እንደገና ተዋቀረ። ፌብሩዋሪ 9, 2021 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 221-26 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 220-26 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜጎች መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| **1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ** | **በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ** |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| **ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** ** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org